# ጉሮ ወሸባዬ ጉሮ ወሸባ

ያ የሮሙ ጀግና አበበ በቂላ
በባዶ እግሩ ሮጦ ድል ሲያበስር ለኛ

ዳግሚያ ድል ነበረ ለኢትዮጵያ ሃገሬ
ሚስጥሩ ሲፈታ ቅኔው በዝማሬ

እንዲህ ነው ማሸነፍ ቃታነን ሳይስቡ
ማንነት ማሳወቅ ለዓለም በሙሉ

አገሬ ኢትዮጵያ የታሪክ ማህደር
ስንክሳር ሳይከፈቱ ሳያውቁ መዳፈር

ፋሲል ላሊበላ አክሱም ሕንፃ ውሉ
ሐረር ግንብ ሶፍ ዑመር እስኪ ይናገሩ

ያንብቡ ይቀኙ ሰሙን እያንብቡ
ውስጠ ሚስጥር አላት ገባ ብለው ስያዩ

ከፎቅ መንኮራኩር ከባቡር ከአየሩ
ዛሬነን ብቻ አይተው ትላንትን እረሱ

ልጆችዋ የቁርጥ ቀን
መቸ ይቻላሉ በአንድ ከተመሙ

በአለም ከተማ በለንደን በዙሪያ
የዓለም ዘር አወቀ እትዮጵያን እማማ

ልጆችዋ ቆፍጣና መሸነፍ አይወዱ
እምነት ከልባቸው ድልን የሚያርዩ

ሲመኙ ሲነሱ ድልነን ሊያበስሩ
አለ ከልባቸው ቁጭት መረሳቱ

የስልጣኔ ምንጭ የሰው ልጅ መገኛ
ኢትዮጵያ መሆንዋን አውቀው ከረሱማ

የለም የለም አለች ጥሩየ በቃልዋ
የማራቶን ጀግና ገላኔ ደፋርዋ

የነጭ ጥቁር ዘር በጣም ተደመመ
የኢትዮጵያ ሃገሬን ባንዴራዋን ያዘ

የንግስት ሃገር ናት የጣይቱ ምሪት
ተክሊሏነን ደፋች ኢትዮጵያ ሃገሬ በኪውንዋ ፊት

ሰለራዕብ ቸነፈር የዓለም ዘር ሲያወራ
እረስቶት ማለፉን ገብቶ በዚህ ጎራ

ያራሱን ረስቶ ሌላውን አንኩዋሶ
መኖር ድሮ ቀረ ታሪክ አድበስብሶ

ኢትዮጵያዊ ኩሩ አንገቱን ያልደፋ
ቀና ቀና ይላል ከእንግዲህ ወዲያማ

የአለማየሁ አፅሙ ጮኻ አስተጋባ
ፎከረ ሸለለ ፈንቅሎ ሊወጣ

ተነሳ መንፈሱ ታየ እያገሳ
ከባለድሎች ጋር ሃገሩ ሊገባ

ወገን ተሰነየ በኩራት ተሞላ
ድሌ ማታ ማታ ገና አለ አለ ገና ገና

ድህነት አይደለም የኛ ታሪክ ፋና
ኢትዮጵያ ኢይደለች ወይ የሰው ልጅ አሻራ

ከእንግዲህ አንድ እንሁን ተነስተን በደቦ
ማንነትም ይታይ ልማቱ አብቦ

መፋተጉ ይራቅ እርስ በርስ መናቆር
ለማን ደስ ይበለው ኧረ ለኛም አይበጅ

ኢትዮጵያ ታበፅህ ህዴጎ አበ እግዚአብሔር
ዘመኑ አሁን ነው በአንድ እንዘምር

እገራችን ታብብ ይመር አዝመራዋ
ልማትዋ ጎምርቶ ከፍ ይበል ማንነትዋ

ጉሮ ወሸባየ ወሸባ ጀግና ድል አርጎ ሲገባ
የአገሬ ሰው ይበል እድሜ ለልጆችዋ

ምስጋና ይድረሰው ለአብራክ ለክፋይዋ
ትኑር ለዘላለም ኢትዮጵያ የኛዋ ።

ተዘራ አሰጉ / ከምድረ እንግሊዝ ፥ለንደን ። /